በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# እምነትና ሥራ


## መምህር፡ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

**ነሐሴ ፳ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.**

# እምነትና ሥራ

- "መዳን በእምነት ብቻ ነው" የሚለው የፕሮቴስታንቶች የድኅነት መፈክር ነው፡፡ይህም አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ለብቻ ነጥሎ የመጠቀምን አደገኛነት የሚያመለክት ነው፡፡

## *እምነት ለመዳን የመጀመሪያው ደረጃ ነው*

- ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ "እንግዲህ እኔ እንደሆንሁ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ፡፡" *ዮሐ 8፡24፡፡* "ያመነ የተጠመቀም ይድናል፡፡" ብሏል፡፡ *ማር 16፡16፡፡*

- እምነት ለመዳን የመጀመሪያው ደረጃ ቢሆንም ብቸኛው ጉዳይ ግን አይደለም፡፡

*ምሳሌ 1*

- አረጋዊው ስምዖን ሕፃኑን ጌታችንን ታቅፎ "ጌታ ሆይ፥ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ፤ ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና" *ሉቃ 2፡29-30፡፡* ቢልም ከሠላሳ ሦስት ዓመት በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከበረ ደሙ ፈሳሽነት የፈጸመውን ማዳን ግን አላየም ነበር፡፡

- አረጋዊው ስምዖን ያየው የጌታችንን ልደት ነበር፡፡ ነገር ግን ሰው መሆኑ ወደ መዳን የሚያደርስ የመጀመሪያ ደረጃ በመሆኑ የተነሳ ያለመጠራጠር "ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋል፡፡" አለ፡፡

- ሰውን በማዳን ጉዞ የመጀመሪያ የሆነው የጌታችን መወለድም በዚህ ክፍል ሁሉንም ሂደት የሚገልጽ ሆኖ ተቀምጧል፡፡ ታዲያ ይህ ማለት በመወለዱ ብቻ ድነናል ማለት ነው? አይደለም ምክንያቱም "ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም፡፡" ተብሎ ተጽፎልናልና፡፡ *ዕብ 9፡22፡፡*

# እምነትና ሥራ…

*ምሳሌ 2*

- ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ ሲላስ ለእስር ቤት ጠባቂው "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" *የሐዋ ሥራ 16፡31።* አሉት።

- ታዲያ በርሱ እምነት ብቻ ቤተሰቡ ሁሉ እንዴት ሊድን ይችላል? የአንዱ ሰው እምነት ሌላውን ሰው ሊያድነው ይችላል?

- ትክክለኛው ትርጉሙ የወህኒ ቤት ጠባቂው እምነት ለራሱ መዳን የመጀመሪያ ደረጃ እንደሆነ የሚያስረዳ ነው።

- የመጀመሪያ ደረጃ የሆነው የእርሱ ማመን ቤተሰቡ በሙሉ ወደ እምነቱ እንዲገቡ የሚጠቅም ቤተሰቡንም ሁሉ ወደ ድኅነት የሚመራ መልካም ጅማሬ ነበር።

- ይህም በሚከተለው ጥቅስ ተገልጿል። "ለእርሱና በቤቱም ላሉት ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ተናገሩአቸው። በሌሊትም በዚያች ሰዓት ወስዶ ቍስላቸውን አጠበላቸው፥ ያን ጊዜውንም እርሱ ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር ተጠመቀ።" *የሐዋ ሥራ 16፡32-33።*

- የወህኒ ቤት ጠባቂው እምነት ለቤተሰቡ ሁሉ መዳን ምክንያት የሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስ ሌላውንም (የቤተሰቡን እምነትና ጥምቀት) ደረጃ ሳይቀንስና ሳያጠፋ ሁሉን ሂደት የሚገልጽ አድርጎ ተጠቅሞበታል።

# እምነትና ሥራ…

*ምሳሌ 3*

- ጌታችን ዘኬዎስን “ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖለታል፡፡” አለው፡፡ *ሉቃስ 19፡9፡፡*
- ጌታችን ለዘኬዎስ ይህን የተናገረው ዘኬዎስ ያለአግባብ ከሌሎች የወሰደውን ሁሉ አራት እጥፍ አድርጎ ሊከፍል ቃል ሲገባ ነው፡፡ ጌታችን የተናገረው ቃል የሚያስገነዝበን የዘኬዎስ ንሥሐ ለቤተሰቡ ሁሉ መዳን የመጀመሪያ ደረጃ እንደሆነ ነው፡፡ ነገር ግን ንስሐ ብቸኛው ደረጃ አይደለም፡፡
- ቤተሰቡ በሙሉ ንስሐ መግባትና ማመን አለበት፡፡ ከሁሉም በላይ በመስቀል ላይ በሚፈሰው ደሙ ስለሚፈጸመው ማዳኑ የገባው ቃል ያረጋገጠው ይህን ነውና፡፡

*ምሳሌ 4*

- ቅዱስ ጳውሎስ “እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፡፡” *ሮሜ 5፡1፡፡* ቅዱስ ያዕቆብም “ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ፡፡” *ያዕ 2፡24፡፡* በማለት ጽፈዋል፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ የመጀመሪያውን ደረጃ እምነትን ሁሉንም ሂደት ለማመልከት የተጠቀመበት ሲሆን ቅዱስ ያዕቆብ ደግሞ እምነት ብቻውን እንደማያጸድቅ ገልጦልናል፡፡

# <u>እምነትና ሥራ…</u>

<u>*ምሳሌ 5*</u>

- ቅዱስ ጳውሎስ ጌታችን ተገልጦለት "የኃጢአትንም ስርየት <u>*በእኔም በማመን*</u> በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ፥ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ዓይናቸውን ትከፍት ዘንድ፥ ከሕዝቡና ወደ እነርሱ ከምልክህ ከአሕዛብ አድንሃለሁ።" እንዳለው ነግሮናል። <u>*የሐዋ ሥራ 26፡18።*</u>
- *በሌላ ክፍል* "… ንስሐ ይገቡ ዘንድና ለንስሐ የሚገባ ነገር እያደረጉ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ይሉ ዘንድ ተናገርሁ።" አለ። <u>*የሐዋ ሥራ 26፡19-20።*</u>
- በመጀመሪያ እምነት ቀዳሚው ደረጃ ሆኖ የተጠቀሰ ሲሆን በሁለተኛው ክፍል ደግሞ እምነት ብቻውን ሳይሆን ሌሎችም (ንስሐ/ ወደ እግዚአብሔር መመለስ/ መልካም ሥራ) ደረጃዎች ለመዳን አስፈላጊነታቸው ተገልጿል።

<u>*ምሳሌ 6*</u>

- ቅዱስ ጳውሎስ "የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና።" ብሏል። <u>*ሮሜ 10፡13።*</u> ይህንን ያነበበ ሰውም ያመነ ሁሉ የሚድን ሊመስለው ይችላል። ነገር ግን ጌታችን "በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።" በማለት የሥራንም አስፈላጊነት ነግሮናል። <u>*ማቴ 7፡21።*</u>
- ስለዚህ እምነት የመጀመሪያው ደረጃ ሆኖ ሕግጋቱን መጠበቅ ተከታዮቹ ደረጃዎች እንደሆኑም ተጽፎልናል። <u>*ማር 10፡18-27፤ ሉቃስ 18፡18-27።*</u>

# እምነትና ሥራ…

*ምሳሌ 7*

- ጌታችን ስለ ልባሞቹና ሰነፎቹ ደናግል ምሳሌ ከተናገረ በኋላ "ቀኒቱንና ሰዓቲቱን አታውቁምና እንግዲህ ንቁ።" አለ። *ማቴ 25፡13።*

- ይህንን ከሰነፎቹ ደናግል አንጻር እስኪ እንመልከት። መንቃት በጌታችን የተጠቀሰ ብቸኛው ቁምነገርና ለመዳን የመጀመሪያው ደረጃ ቢሆንም የመጨረሻው ግን አይደለም።
  - 1ኛ ደረጃ፡- መንቃት
  - 2ኛ ደረጃ፡- ዘይት የሌለን መሆኑን ማስተዋል
  - 3ኛ ደረጃ፡- ልባሞቹን ደናግል እንዲረዱን መጠየቅ
  - 4ኛ ደረጃ፡- ምክራቸውን በመቀበል በፍጥነት ዘይቱን ለመግዛት መሄድ
  - 5ኛ ደረጃ፡- ሙሽራው መጥቶ በሩን ከመዝጋቱ በፊት ተመልሶ መድረስ

- እነዚህ ሰነፎቹ ደናግል የመጀመሪያው ደረጃ መንቃትን ለመዳን የሚያስፈልግ ብቸኛው ደረጃ እንደሆነ በመቁጠር ሌላውን ሁሉ ትተው በንቃት ቢጠብቁ ሰነፎች ተብለው አይጠሩም ይሆን? እንደዚሁ ለመዳን የሚያስፈልግ ብቸኛ ደረጃ እምነት ብቻ ነው የሚልም ሰው ሰነፍ ይባላል። "አንተ ከንቱ ሰው፥ እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን?" እንደተባለ። *ያዕቆብ 2፡20*

- እምነትን ከሥራ መለየት ነፍስን ከሥጋ እንደ መለየት ነው። ውጤቱም ሞት ነው። "ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።" *ያዕ 2፡26።*

- ቅዱስ ያዕቆብ መልካም ሥራን ከነፍስ፤ እምነትንም ከሥጋ ጋር ያለማዘዋወር ማገናኘቱስ ምን ያህል ድንቅ ነው!!!

# ንስሐና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

- ፕሮቴስታንቶች ንስሐ አንዱ የጸጋ ሥራ አድርገው ሲቆጥሩት ሰው ባይሻውም በኢየሱስ እግር ሥር ራሱን ከጣለ ከኃጢአቱ ነጻ ይወጣል ይላሉ።

- በኦርቶዶክሳዊ እምነት የሰው መንፈሳዊ ሕይወት ሁሉ ከመንፈስቅዱስ ጋር ኅብረት ያለው ነው። መንፈስቅዱስ በጎን እንድናደርግ ቢረዳንም መሻት ግን ያስፈልገናል። መሻት የሌላቸውንም ሐዋርያው "ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም" በማለት ይወቅሳቸዋል። *ዕብ 12፡4።*

- ቅዱስ መጽሐፍ መንፈሳዊ ሕይወትን የእግዚአብሔር የጦር ዕቃ የሚያስፈልገው ትግል እንደሆነ "መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዥዎች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ።" በማለት ያስረዳናል። *ኤፌሶን 6፡12።*

- ሰው ይህንን ጦርነት ያለ ጥርጥር ተዋግቶ ማሸነፍ ይጠበቅበታል። እርሱም ሥራ ነው።

- ይህም ውጊያ ጌታችን ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መላእክት/አለቆች በላከው መልዕክቱ "ድል ለነሣው ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ፥ ነጭ ድንጋይንም እሰጠዋለሁ" *ራእ 2፡17።* እንዳለው የራሳችንን መወጣት ይጠበቅብናል። "ወደ እኔ ተመለሱ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፥ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር" ያለንም ለዚሁ ነው። *ዘካ 1፡3።*

# <u>በደሙ ለመዳን የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች</u>

- ከሚያስፈልጉት ቅድመ ሁኔታዎች ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ይገለፃሉ፡፡
    1. እምነት
    2. ጥምቀት
    3. የቤተክርስቲያን ምስጢራት
    4. መልካም ሥራ

*<u>1. እምነት</u>*

- "እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው፡፡" *<u>ዕብ 11፡1፡፡</u>*

- "እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል፡፡ አንተ ከንቱ ሰው፥ እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን?" *<u>ያዕ 2፡19-20፡፡</u>*

- "ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ፡፡" *<u>1ኛ ቆሮ 13፡2፡፡</u>*

# በደሙ ለመዳን የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

*2. ጥምቀት*

- ምስጢረ ጥምቀት ከጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚፈጸም ነው፡፡ ይህም "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡" በሚለው ቃሉ የተደገፈ ነው፡፡ *ማቴ 28፡19-20፡፡*

*3. የቤተክርስቲያን ምስጢራት*

- የተጠመቁ ከጥምቀታቸው፤ ንስሐ የገቡ ከቀኖናቸው በኋላ ፤ የጋብቻ ምስጢር የተፈጸመላቸውም… ቅዱስ ቁርባን መቀበል ይኖርባቸዋል፡፡

*የቅዱስ ቁርባን ጥቅሞች*

1. የኃጢአት ሥርየትና ድኅነት
   ሁላችንም ዘወትር እንበድላለን፤ ዘወትርም በጌታችን ደም ከኃጢአታችን መታጠብ ይኖርብናል፡፡ "የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል፡፡ … ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም፡፡" *1ኛ ዮሐ 1፤8-10፡፡*

2. በቃልኪዳኑ መሠረት በርሱ ለመኖር መቻል
   "*ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ፡፡*"
   *ዮሐ 6፤53-58፡፡*

# የቅዱስ ቁርባን ጥቅሞች...

3. ዘላለማዊ ሕይወት
   "*ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።*" *ዮሐ 6፥54 እና 58።*

4. በመንፈሳዊ ሕይወት ማደግ፤ መንፈሳዊ ብቃት ማግኘትና በርሱ ሕያው መሆን
   "*ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና። ሕያው አብ እንደ ላከኝ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን፥ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል።* " *ዮሐ 6፥55 እና 57።*

5. በቅዳሴ እንደተገለጸው ለነፍሳችን፤ ለሥጋችንና ለመንፈሳችን መታደስን ይሰጣል

*ቅዱስ ቁርባን ከመቀበላችን በፊት የሚያስፈልጉ ጥቂት ቅድመ ሁኔታዎች*

- ኦርቶዶክሳዊ መሆንና ኅብስቱ ወደ እውነተኛ ሥጋነት ወይኑም ወደ እውነተኛ ደምነት እንደሚለወጥ ማመን። "ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፥ ቆርሶም። እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው" *1ኛ ቆሮ 11፡24።*
- ዘወትር የሚናዘዝና ንስሐ በመግባት ኃጢአትን በመተው የሚኖርና ለዚሁም የንስሐ አባት ያለው መሆን።
- የተጣለውን የታረቀ መሆን "እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፥ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፥ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፥ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ። አብረኸው በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ፤ ባላጋራ ለዳኛ እንዳይሰጥህ ዳኛም ለሎሌው፥ ወደ ወህኒም ትጣላለህ፤ እውነት እልሃለሁ፥ የመጨረሻዋን ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ ከቶ ከዚያ አትወጣም።" *ማቴ 5፡23-24።*
- ቅዳሴ የሚያስቀድስና ቃለ እግዚአብሔርንም የሚማር መሆን

# መልካም ሥራ

- ኦርቶዶክሳውያን ሰው ጌታችን “ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም” በማለት *ዮሐ 15፡5* እንዳስተማረን መልካም ሥራን መሥራት እንድንችል የመንፈስቅዱስ እርዳታ እንደሚያስፈልገን መረዳት ይኖርብናል፡፡
- “እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል፡፡ አንተ ከንቱ ሰው፥ እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን?” *ያዕ 2፡19-20፡፡*
- በእኛ ላይ የሚሆነው ፍርድ እንደ ሥራችን ይሆናል፡፡ ማቴ 25
- ልበ አምላክ ዳዊት “አቤቱ፥ ምሕረትም ያንተ ነው አንተ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ፍዳውን ትሰጣለህና፡፡” ብሎአል፡፡ *መዝ 62፡12፡፡*
- “እግዚአብሔር ሥራን ሁሉ የተሰወረውንም ነገር ሁሉ፥ መልካምም ቢሆን ክፉም ቢሆን፥ ወደ ፍርድ ያመጣዋል፡፡” *መክ 12፡14፡፡*
- “የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና፤ ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ያስረክበዋል፡፡” *ማቴ 16፡27፡፡*
- “ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና የምትደላደሉ፥ የማትነቃነቁም፥ የጌታም ሥራ ሁልጊዜ የሚበዛላችሁ ሁኑ፡፡” *1ኛ ቆሮ 15፡58፡፡*

# መልካም ሥራ ለእምነት የሚያስፈልግ ፍሬ ነው

- “ቃሉ የታመነ ነው። እግዚአብሔርንም የሚያምኑት በመልካም ሥራ በጥንቃቄ እንዲጸኑ፥ እነዚህን አስረግጠህ እንድትናገር እፈቅዳለሁ። ይህ መልካምና ለሰዎች የሚጠቅም ነው፤ ከወገናችንም ያሉት ደግሞ ፍሬ ቢሶች ሆነው እንዳይቀሩ፥ የግድ ስለሚያስፈልገው ነገር በመልካም ሥራ እንዲጸኑ ይማሩ።” *ቲቶ 3፡8 እና 3፡14።*

- “አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን? እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ፥ በሥራም እምነት እንደ ተፈጸመ ትመለከታለህን” *ያዕ 2፡21-22።*

- “መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።” *ማቴ 5፡16።*

- “ነገር ግን በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል” *ሮሜ 2፡10።*

- “እንግዲህ በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው።” *ያዕ 4፡17።*

# <u>የምንድነው መች ነው?</u>

- መዳን የዕድሜ ልክ ሂደት ሲሆን በጾም፤ በጸሎት፤ በምስጋና፤ በንስሐ… መታጠር አለበት። ዘወትር በጦርነት ውስጥ ነን ውጤቱም አይታወቅምና ሰው የመጀመሪያውን ውጊያ አሸንፎ በአሥራ ሁለተኛው ሊሸነፍ ይችላል። ማንም እስኪፈጽም ድረስ ስለ ውጤቱ እርግጠኛ ሊሆን አይችልም። *ማቴ 24፡13።*

- ቅዱስ ጳውሎስ "በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ።" እንዳለ *ፊል 2፡12*

- ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንደነገረው ጳጳሳትም እንኳ ቢሆኑ መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል። "ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፥ በእነዚህም ጽና፤ ይህን ብታደርግ፥ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና።" እንዳለ። *1ኛ ጢሞ 4፡16*

- ቅዱስ ጴጥሮስም "ጻድቅም በጭንቅ የሚድን ከሆነ ዓመፀኛውና ኃጢአተኛው ወዴት ይታይ ዘንድ አለው? " ብሎናል። *1ኛ ጴጥ 4፤18።*

- ቅዱስ ጳውሎስም "… የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ።" *ዕብ 12፡1።*

- "እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል" *ማቴ 24፡13።*

# ማጠቃለያ

- ማንኛውም እምነትን ከሥራ ነጥሎ የሚሰብክ ስነፍና ሞትንም የሚሰብክ ነው፡፡ “ እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ ነውና ” *ያዕ 2፡20፡፡*

- በርግጥም “እምነት አለኝ የሚል፥ ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን? ” ብሎናል፡፡ *ያዕ 2፡14፡፡*

- እምነት ሥራ ካለው እምነቱም ሥራ ያሆናል፡፡ bእምነትም የምንሠራው እግዚአብሔር ያዘዘንን የእግዚአብሔር ሥራ ነው፡፡ *ዮሐ 6፡28-29፤ ዮሐ 5፡36፡፡*

*እምነትና ሥራ*

- የንስሐ ሕይወት ነው
- መንፈሳዊ ትግል ነው
- የቅድስና ሕይወት ነው
- እምነት የሚሠራው በፍቅር ሲሆን ነው
- አገልግሎት ነው

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

ይቆየን።